## ከቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የሰሜን አሜሪካ

## የልኡካን ቡድን የተሰጠ መግለጫ

መስከረም 11 ቀን፣ 2000 ዓ.ም

ዋሽንገተን ዲሲ

የቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ የሰሜን አሜሪካ ልኡካን ቡድን ጳጉሜ 4/1999 ዓ.ም ዋሺንግተን ዲሲ ገብቶ በድርጅቱ ምክር ቤት የተሰጠውን ሀላፊነት እየተወጣ ይገኛል::ይሁን እንጂ የድርጅቱ ሊቀመንበር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል በእለቱ ከልኡኩ ጋር ባለመምጣታቸውና በቀጣይ የልኡካን ቡድኑ እንቅስቃሴዎችም ባለመሳተፋቸው አንዳንድ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች በድርጅቱ ደጋፊዎች ዘንድ በመፈጠሩ ይህንን አጭር ማብራሪያ መስጠት አስፈልጉአል::

በቅድሚያ ይህ ቡድን ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የፓርቲው ሊቀመንበር መሆናቸውን እንዲሁም የዚህ ልኡክ መሪ እንዲሆኑ በምክር ቤታችን መመረጣቸውን እንደሚቀበልና አለመቀበልም እንደማይችል በማረጋገጥ ከጉዳዩ ጋራ ተያያዥነት ባላቸው ነጥቦች ዙሪያ ያለውን እውነታ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቧል::

- የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ለተለያዩ ድርጅት ነክ ስራዎች (በውጭ አገር የሚገኘውን በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተ ችግር መፍታት አንዱ ነው) ወደ ውጭ አገር ልኡካንን ለመላክ የወሰነው ያለ ምንም ተቃውሞ ነው:: ለችግሩ መፍትሄ ይሆን ዘንድም ልኡካኑ ከመሄዳቸው አስቀድሞ በቅንጅት ስም አለም አቀፍ አመራር ለመስጠት ተቋቁመል የተባሉትን ሁለቱንም ድርጅቶች ከእስር የተፈቱት የአመራር አባላት በሙሉ ድምጽ አፍርሰዋቸዋል:: ይህንንም በሊቀመንበሩ ፊርማ በተጻፈ ደብዳቤ ለሚመለከተው ሁሉ አስታውቀዋል:: ወደ ውጭ አገር የሚሄዱት የልኡካን አባላትም በሙሉ ድምጽ በምክር ቤቱ ተመርጠዋል ይህም በሊቀመንበሩ በተጻፈ ደብዳቤ ለሚመለከተው ሁሉ ተገልጧል::
- የልኡካን ቡድኑ በውጭ አገር በሚቆይበት ጊዜ የሚሰራውን ስራ፣የውሳኔ አሰጣጥ ደንብ፣ በውጭ አገር የሚገኙ የድርጅቱ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለወደፊት የሚኖራቸውን የዴሞክራሲያዊ አወቃቀር መልክ በዝርዝር ተወያይቶና አጽድቆ የቡድን አባላትም ይህንን ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶቹ ጋር በመመካከር እንዲያስፈጽሙ ወስኖአል::
- በተለይ በሰሜን አሜሪካ የነበረውን የልኡካን ቡድን የስራ ፕሮግራምና ይህንንም ፕሮግራም የማስፈጸሙን ተግባር ከሊቀመንበሩ በቀረበ ሀሳብ ከሁለቱም ወገን ነጻ በሆነ ወገን እንዲከናወን በሙሉ ድምጽ ወስኖአል::
- የልኡካን ቡድኑ ወደ ውጭ ከመሄድ እንዲቆይ ከሊቀመንበሩ በተለያየ ጊዜ የቀረበው ሀሳብ ለድምጽ ቀርቦ በከፍተኛ የድምጽ ልዩነት ወድቆዋል::
- ሊቀመንበሩ በተለያዩ ምክንያቶች (በዋናነት በጤናቸው ችግር ምክንያት) ከልኡካን ቡድኑ ጋር ለመሄድ እንደማይችሉ አሳወቁ:: ምናልባት አሜሪካን ሀገር ከሄዱም በግል ለህክምና እንጂ የቡድኑ አካል እንደማይሆኑ ገለፁ:: ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ የተደረጉት ጥረቶች በሙሉ አልተሳኩም:: የመጨረሻው ሙከራ (የልኡካን ቡድኑ አዲስ አበባን ከመልቀቁ አንድ ቀን በፊት) ባይሳካም ሊቀመንበሩ በመሪነታቸው በውጭ ለሚገኙ የድርጅቱ ደጋፊዎች የቡድኑ ስራ የተሳካ እንዲሆን መልእክት እንዲያስተላልፉ ቢጠየቁም ፈቃደኛ አልሆኑም::
- ሊቀመንበሩ የልኡካን ቡድኑ አሜሪካን አገር ከገባ በሁዋላ ሀሳባቸውን መቀየራቸውንና ወደ አሜሪካ ለመምጣት መወሰናቸውን ከአስተባባሪ ኮሚቴው ሰማ:: ወዲያዉኑ አዲስ አበባ ድረስ በመደወል ይህ እዉነት መሆኑን ከሊቀመንበሩ እንዳረጋገጠ ደስታውን በመግለጽ፣ የሚመጡት የልኡካን ቡድኑ መሪ በመሆን እና በቡድኑ ስራ ለመሳተፍ እንደሆነ ፣ በፕሮግራም ዙሪያ ለመነጋገርና እሳቸውም በፕሮግራሙ በሙሉ ለመሳተፍ ይችሉ እንደሆን (ከጤና ጋር በተያያዘ ችግር ሊኖር እንደሚችል በመገመት) ለመጠየቅ ያደረገው የስልክ ሙከራ ከእናንተ ጋር የምነጋገረው የለም በሚል አጭር መልስ ተገታ::
- ከዚያ በሁዋላ ከአስተባባሪ ኮሚቴው ጋር ባደረጉት ግንኙነት የሚመጡበትን የራሳቸውን ፕሮግራም ዝርዝር ቢያሳውቁም የልኡካን ቡድኑ አስተባባሪ ኮሚቴው ከድጋፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን ያወጣውን ፕሮግራም በሚመለከትና እሳቸውም የልኡካን ቡድኑ መሪ ሆነው ለመስራት ያስቡ እንደሆን ለመጠየቅ ያሉበትን ስልክ በመፈለግ በቴሌ ኮንፍረንስ ለማነጋገር ቢሞክርም ፈቃደኛ አልሆኑም:: ከምክትል ሊቀመንበሩዋ ጋር ባደረጉት አጭር ንግግር ግን እዚያው ዋሽንግተን ዲሲ ስመጣ እንነጋገራለን ከማለት በስተቀር የልኡካን ቡድኑ አካል ለመሆን ፍላጎት እንዳላቸዉም ለመናገር ፈቃደኛ አልነበሩም::
- ይህም ሆኖ በአስተባባሪ ኮሚቴው አባላት በእሁዱ ፕሮግራም ላይ እንዲገኙና አጭርም ቢሆን መልእክት እንዲያስተላልፉ ተጠይቀው እስከ ፕሮግራሙ መጀመሪያ ድረስ ይመጣሉ ተብሎ ተጠብቀው ነበር፡ አልመጡም::
- በልኡካን ቡድኑ እምነት ሊቀመንበሩ አሁንም የቡድኑ መሪ ሆነዉ፣ የድርጅቱን ውሳኔዎች አክብረውና በድርጅቱ ህግና ደንብ መሰረት ስራቸውን ለማከናወን እስከፈቀዱ ድረስ ሁልጊዜም በደስታ እንቀበላቸዋለን ብቻ ሳይሆን ይህን ለመከልከልም ምንም ስልጣን እንደሌለን እናዉቃለን:: ወደፊትም ቢሆን በቡድን መሪነት የምክር ቤቱን ውሳኔ ለመፈጸም አብረውን ይሳተፋሉ ይሰራሉ ብለን እንጠብቃለን::